# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org



አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!




ግንቦት 7 የትብብር ጥሪ ሲያደርግ ሁላችንም በአገር ማዳን ስሜት እንነሳ በሚል ብቻ አይደለም። የተለያዩ ርዕዮቶች እና አስተሳሰቦች ባላቸው ቡድኖች መካከልም ትብብር ሊኖር እንሚችል ግንቦት 7 ያምናል። በአንድ ድርጅት ውስጥ እንኳን የተለያዩ አስተሳሰቦችን የሚያራምዱ ቡድኖች ቢኖሩ ከእያንዳንዱ ጋር መተባበር ይቻላል ብሎ ያምናል።

ግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባርና የግንቦት 7፣ ለፍትህ፣ ዴሞክራሲና የነጻነት፣ ንቅናቄ መሀል የተደረገውን ውህደት በተመለከተ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ፣

ዛሬው ዕለት፣ ጥር 2 ቀን 2007 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባርና የግንቦት 7፣ ለፍትህ ለዴሞክራሲና የነጻነት፣ ንቅናቄ፣ ድርጅቶች፣ ተዋህደን “አርበኞች ግንቦት 7፣ ለአንድነትና ዴሞክራሲ፣ ንቅናቄ”፣ በሚባል ሥም መጠራት መጀመራችንን ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ስናበስር፣ እጅግ ከፍተኛ ደስታ ይሰማናል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ባለፉት በርካታ አስርተ አመታት፣ለፍትህ፣ ለእኩልነት፣ ለነጻነት፣ መብትና አንድነት፣ ከፍተኛ ትግል ሲያካሂድ ቆይቷል። በአደረገውም ትግል እጅግ ከፍተኛ መስዕዋትነት ከፍሏል። ለከፈለው ከፍተኛ ዋጋ የሚመጥን ግን ምንም ዓይነት ውጤት አላገኘም። እንዲያውም ከጊዜ ወደ ጊዜ የመብት ረገጣው፣ አድሎው፣ ማስፈራራቱና ማዋከቡ ተጠናክረው መቀጠል ብቻ ሳይሆን፣ ሀገራችን ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ልትቀጥል የማያስችል ከፍተኛ የመበታተን አደጋ አንጃበባት ትገኛለች።

በሀገራችን ላይ ላንጃበበው ከፍተኛ የመበታተን አደጋ ምክንያት የሆነው በሥልጣን ላይ ያለው የወያኔ የአምባገነን ቡድን ነው። ይህ ዘረኛ አምባገነን ቡድን በሀገራችን ታሪክ በሥልጣን ላይ ከመጡ የገዥ ሃይሎች ጋር ሲወዳደር ሀገርን ለከፍተኛ አደጋ በማጋለጥ፣ ሕዝቧን በማወረድ፣ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ዕኩይ ሃይል መሆኑን በበርካታ ተግባራቶቹ ያለ ምንም ጥርጣሬ አረጋግጧል።

በሌላ በኩል ለቀድሞቹም ሆነ ለዛሬው ዘረኛው የወያኔ አምባገነን ገዥ በሕዝብና በሀገር ላይ በደል እየፈጸመ በሥልጣን መቆየት የቻለበት ምክንያት፣ በተቃዋሚነት የሕዝቡን ትግል ለመምራት የተንቀሳቀስን ድርጅቶች፣ የተቋቋምንበት ዓላማ መለያዬት ብቻ ሳይሆን፣ አንድ ዓይነት ዓላማ ያለንም ብንሆን፣ ከድርጅቶቻችን ጠባብ ፍላጎቶችና ስሜቶች ባለፈ፣ የሀገርና የሕዝብን ጉዳይ በማስቀደም በጋራ መሰባሰብና መታገል ስላቃተን ነው። በዚህም ድርጊታችን የራሳችንን ብቻ ሳይሆን የወገናችንንም የመከራ ዘመን እያራዘምን እንገኛለን።

ይህ ሁኔታ በተለያዩ ተቃዋሚ ድርጅቶች መሀል ከፍተኛ ጥርጣሬና ፍርሀት ከመፍጠሩ የተነሳ በምንም ዓይነት ሁኔታ፣ ተቃዋሚ ድርጅቶች በጋራ በሀገርና በሕዝብ ደረጃ ትርጉም ያለው ስራ መስራት አይችሉም፣ የሚለው አመለካከት የበላይነት እንዲያገኝ አድርጎታል።

በዛሬው ጥር 2 ቀን 2007 ዓ.ም ወደ ውህደት የመጣነው፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባርና የግንቦት 7፣ ለፍትህ፡፡ ለነጻነትና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ መዋሃድ መወሰናችንን፣ ስንገልጽ በተናጠል ከሚደረጉ በጋራ የሚደረጉ የትግል ጥረቶች ውጤታማ ይሆናሉ በሚል ብቻ ሳይሆን፣ የተቃዋሚ ድርጅቶች፣ በምንም ዓይነት ሁኔታ በሀገርና በሕዝብ ደረጃ ትርጉም ያለው ሥራ በጋራ መስራት አይቻሉም የሚለውን፣ አስከፊ ተመክሮና አመለካካት ለመስበርም ነው።

.በእኛ እምነት ከትናናሽ ድርጅቶች ዙሪያ ከሚሽከረከሩ ሀሳቦችና ስሜቶች ለመውጣትና ሀገራዊና ሕዝባዊ የሆነው ጉዳይ ለማስቀደም የወሰነ ማንኛውም ድርጅት፣ ... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ግንቦት 7ና አርበኞች ግንባር ያደረጉት ውህደት የኢትዮጵያውያንን ከፍተኛ ድጋፍ እያገኘ ነዉ

ዘረኛውንና ከፋፋዩን የወያኔ አገዛዝን ከኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ለማስወገድ በተለያዩ መንገዶች ሲታገሉ የቆዩት ሁለቱ ድርጅቶች ግንቦት 7 እና የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር በጥር 2 ቀን 2007 አ.ም በኤርትራ በተካሄደው ስምምነት ውህደቱ በደማቅ ስነስርአት መፈጸሙን ዘጋቢያችን ከስፍራው ያደረሰን መረጃ ያመለክታል። በኤርትራ ከተካሄደው ጉባየ ቀደም ብሎ የግንቦት 7 ንቅናቄ በሁሉም የአለም አህጉራት ማለትም አፍሪካን ጨምሮ በአውሮፓ፤ ኤስያና ሰሜን አሜሪካ ከሚገኙ አባላቶቹ ጋር በጉዳዩ ዙሪያ ስፊ ምክክር ማድረጉ የተመለከተ ሲሆን ውህደቱ በሁሉም አባላት ዘንድ በሙሉ ድምጽ ይሁንታን አግኝቶ ውሳኔ መተላለፉን የደረሰን መረጃ ያሳያል። በኤርትራ በተካሄደው በዚህ ታርካዊ ስምምነት ከመላው አለም የተሰባሰቡ በርካታ የድርጅቶቹን አመራሮች ጨምሮ የሌሎች ድርጅት ተወካዮች በክብር እንግድነት የተገኙ ሲሆን በመስራች ጉባየ አባላት ይሁንታን አግኝቶ የተመሰረተው አዲሱ ድርጅት አርበኞች ግንቦት 7 ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ (አግኤደን) የሚል መጠሪያ እንደተሰጠው ለማወቅ ተችሏል።

በኢትዮጵያ የነፃነት ትግል መድረክ ተጨባጭ ለውጥ እንደሚያመጣ የተነገረለት ይህ ውህደት ከፋሺስታዊው አጋዘዝ ጋር በመሬት ላይ ለሚደረገው የትጥቅ ትግል ማርሽ ቀያሪ መሆኑ ተነግሯል። በጉባየው የተገኙት የአርበኞች ግንባር ሊቀመንበር አርበኛው መኣዛ ጌጡ የውህዱን እውን መሆንና አገራዊ ጠቀሜታውን ያጎላ ንግግር ያደረጉ ሲሆን በተናጥል እየተደረገ ያለው ትግል ስንዝር ወደ ፊድ ማራመድ እንደማያስችል በመረዳት ውህደቱ መፈጸሙን ታሪካዊና ለኢትዮጵያም ህዝብ አንድ የድል ምዕራፍ ያለው ክስተት ነው ሲሉ ገልጸውታል። የግንቦት 7 የፍትህ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ በበኩላቸው እንኳን ደስ ያላችሁ፤ በጉባያችሁ ላይ መገኘት ባልችልም ከዚህ በኋላ በየትኛውም እንቅስቃሴ ከጎናችሁ ታገኙኛላችሁ ሲሉ ቃል የገቡ ሲሆን ይህ ውህደቱ በስልጣን ላይ ያለውን ዘረኛውን የህወሃት አገዛዝ ማስወገድ ብቻ ሳይሆን ቀጣይ ለሚመሰረተው ዲሞክራሲያዊ ..... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## አርበኞች- ግንቦት 7 ለኢትዮጲያ ህዝብ፣ ለመላከያ ሰራዊቱና ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ጥሪ አቀረበ

አርበኘኞች ግንቦት ሰባት ንቅናቄ በቅርቡ በግንቦት 7 እና በ አርበኞች ግንባር መካከል የተደረገውን ውህደት አስመልክቶ ባወጣው መግለጫ፤ “እኛ መዋሃድ መወሰናችንን ስንገልጽ፤ በተናጠል ከሚደረጉት – በጋራ የሚደረጉ የትግል ጥረቶች ውጤታማ ይሆናሉ በሚል ብቻ ሳይሆን፣ ”የተቃዋሚ ድርጅቶች፣ በምንም ዓይነት ሁኔታ በሀገርና በሕዝብ ደረጃ ትርጉም ያለው ሥራ በጋራ መስራት አይቻሉም’ የሚለውን፣ አስከፊ ተመክሮና አመለካካት ለመስበርም ጭምር ነው።” ብሏል። ”ከትናናሽ ድርጅቶች ዙሪያ ከሚሽከረከሩ ሀሳቦችና ስሜቶች ለመውጣትና ሀገራዊና ሕዝባዊ የሆነውን ጉዳይ ለማስቀደም የወሰነ ማንኛውም ድርጅት፣ አርበኞችና ግንቦት7፣ እንደደረሱበት የውህደት ውሳኔ፤ ወይም በሌሎች በጋራ ሊያሰሩ በሚችሉ ስምምነቶች አብሮ ለመስራት መወሰን የማይችልበት ምንም ምክንያት አይታየንም።”ብሏል ንቅናቄው።

“በወያኔ አድሎ ስርዓት የተንገፈገፈና ትግሉን ለመቀላቀል የቆረጠ ማንኛውም ዜጋ፣ የተገኘውን አጋጣሚ በመጠቀም ትግሉን መቀላቀል ይችላል”ያለው አርበኞች-ግንቦት 7፤ “የኢትዮያ ሕዝብ በአንድነት የተነሳ ቀን ደግሞ፣ የወያኔ ግብዓተ መሬት ይፈጸማል ብለን ከልብ እናምናለን።” ሲል የመተባበርን አንድነት በ አጽንኦት ገልጿል። ንቅናቄው ለተቃዋሚ ድርጅቶች ባስተላለፈው መልእክት “ዛሬ በአርበኞችና በግንቦት 7፣ የተጀመረው ጉዞ ውጤታማ በመሆን ሀገራዊና ታሪካዊ ትርጉም እንዲኖረው፣ ሌሎችም በተግባር የምትንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ድርጅቶች፣ ወያኔን የማስወገድንና ብሎም ሀገር የማረጋጋቱን ሀላፊነት በጋራ እንድንወጣ የሚያስችል መቀራረብ እንድናደርግ፣ በውህደት በመሰረትነው-በአርበኞች ግንቦት 7፣ ለአንድነትና ዴሞክራሲ፣ ንቅናቄ፣ ሥም፣ ጥሪያችንን እናቀርባለን።” ብሏል።

ንቅናቄው ለወታደራዊና የፖሊስ ሠራዊት አባላት ባስተላለፈው መልእክት ደግሞ፤ ”የወያኔን ዘረኛና አምባገነን ቡድንን .... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## መደማመጥና መነጋገር ከቻልን የማንፈታቸው ልዩነቶች የሉም!!!

(ከዚ ህ በፊት ወጥቶ የነበር የግንቦት 7 ርዕሰ አንቀጽ)

አገራችን እና ሕዝቧ በአንድ ጠባብ ዘረኛ ቡድን መዳፍ ውስጥ ናቸው። በአገራችን የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች የግለሰብም ሆነ የቡድን መብቶቻቸው ተረግጠው በባርነት እየተገዙ፤ ጉልበታቸውና ሃብታቸው እየተመዘበረ ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ የምገኝ ዜጎችና ማኅበረሰቦች ሁሉ እጣ ፈንታችን ተሳስሯል። ሁላችንም ነፃ ካልወጣን በስተቀር ማናችንም በተናጠል የነፃነት አየር መተንፈስ አይቻለንም። ስለሆነም ለራሳችን የግልም የሆነ የቡድን ጥቅም ስንል እያንዳንዳችን ስለሁላችን ማሰብና መጨነቅ ግዴታችን ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ከሁሉም የዲሞክራሲና የነፃነት ኃይሎች ጋር ተባብሮ ለመሥራት የሚያደርገው ጥረት ፍሬ እያፈራ ቢሆንም አሁንም የንቅናቄዓችንን አቋም በትክክል ያልተገነዘቡ ወገኖች እንዳሉ እንገነዘባለን።

ስለሆነም በመሠረታዊ ጉዳዮች ላይ ያለንን አቋም ደጋግመን ግልጽ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል።

**1. ሥልጣንን በተመለከተ**

ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት የሥልጣን ምንጭ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆን ይገባዋል ብሎ ያምናል፤ ለዚህም ይታገላል። ሁሉም የአስተዳደር እርከኖች አንድ ዜጋ አንድ ድምጽ ኖሮት በሚካሄድ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ብቻ የሚሾሙ መሆን ይኖርባቸዋል ብሎ ያምናል፤ ለዚህም ይታገላል።

ግንቦት 7፤ ኢትዮጵያ የተለያዩ ማኅበረሰቦችና የተለያዩ እምነቶች ተከታዮች አገር መሆኗን ያውቃል። ለእንዲህ ዓይነቱ አገር ያልተማከለ ፌደራላዊ የመንግሥት አወቃቀር የተሻለ ነው ብሎ ያምናል። በእያንዳንዱ ፌደራላዊ መንግሥት ውስጥም የዲሞክራሲ መሠረት የሆነው የአንድ ሰው አንድ ድምጽ መርህ መከበር አለበት ብሎ ያምናል።

ይህ መንገድ ነው በብዙሃን የሚደገፉ መሪዎችን ወደ ሥልጣን የሚያወጣልን።

**2. መብቶችን በተመለከተ**

ግንቦት 7፤ የግለሰብና የቡድን መብቶች መከበር ይኖርባቸዋል ብሎ ያምናል፤ ለዚህም ይታገላል።

የቡድን መብቶችን ሰጥቶ የግለሰብ መብቶችን መንሳት ምንም አለመስጠት መሆኑ በተግባር ከመለስ ዜናዊ አገዛዝ የምናየው ነው። መለስ ዜናዊ ለብሄር፣ ብሄረሰቦች የክልል መንግሥታዊ መዋቅርን፣ አርማን፣ መዝሙርን፤ በቋንቋ መማርና መዳኘትን እና የመሳሰሉትን መስጠቱ ዘወትር የሚነግረን ጉዳይ ነው። እነዚህ ሁሉ ዋጋ ያላቸው ነገሮች የሚሆኑት ከግለሰብ ነፃነት መከበር ሆነው ቢሆን ነበር። ሰው የሰውነት ብሎም የዜግነት መብቱ ካልተከበረ የቡድን መብቱ መከበሩ ምን ትርጉም ይሰጠዋል? ፍትህ ሳይኖር በቋንቋው መዳኘቱ ተበዳይን ምን ይጠቅመዋል? የመረጠውን ሰው መሾም፤ የማይስማማውን መሻር የማይችል ከሆነ በስሙ የሚጠራ መንግሥት መኖሩ ምን ይፈይድለታል?

በሌላ በኩል ደግሞ ግንቦት 7፣ የግለሰብ መብቶች ብቻቸው በቂ ናቸው ብሎ አያምንም። እንደ ኢትዮጵያ ላለ ውስብስብ ታሪክ ላላት አገር የቡድን ፍላጎቶችና ስሜቶች በቸልታ ማለፍ አይቻልም። በግለሰብ ነፃነት ሥም የቡድን መብቶችን መደፍጠጥም ኢፍትሃዊ ነው ብሎ ግንቦት 7 ያምናል። በተለያዩ ደረጃዎች ያሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች እና ሃይማኖቶች ጠንካራ የቡድን ስሜትና ፍላጎት ሊኖራቸው እንደሚችል ይገነዘባል።
በዚህም ምክንያት ግንቦት 7 ለሁለቱም የመብት ዓይነቶች እውቅና የሚሰጥ ድርጅት ነው።

**3. ትብብርን በተመለከተ**

ግንቦት 7 የትብብር ጥሪ ሲያደርግ ሁላችንም በአገር ማዳን ስሜት እንነሳ በሚል ብቻ አይደለም። የተለያዩ ርዕዮቶች እና አስተሳሰቦች ባላቸው ቡድኖች መካከልም ትብብር ሊኖር እንሚችል ግንቦት 7 ያምናል። በአንድ ድርጅት ውስጥ እንኳን የተለያዩ አስተሳሰቦችን የሚያራምዱ ቡድኖች ቢኖሩ ከእያንዳንዱ ጋር መተባበር ይቻላል ብሎ ያምናል።

ግንቦት 7፣ የአንድ ወገን እውነት የሁሉም ወገን እውነት ላይሆን እንደሚችል ይገነዘባል። ለመደማመጥ ዝግጁዎች ከሆንን የጋራ ችግሮቻችን በርካታ ናቸውና በሚያስማሙን ጉዳዮች ላይ ተመርኩዘን ትግላችን ማጎልበት ይገባል ብሎ በጽኑ ያምናል፤ ለዚህም ይታገላል።

ግንቦት 7 ከዲሞክራሲና የነፃነት ኃይሎች ጋር መተባበር የሚፈልገው ዛሬ ተባብረን መታገላችን ለዘላቂው አብሮነታችን መሠረት ይጥላል ብሎ ስለሚያምን ነው።

መደማመጥ፣ መሰማማትና መነጋገር ከቻልን የማንፈታቸው ልዩነቶች የሉም።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!**

---

## ታሪካዊው የጣይቱ ሆቴል በእሳት መጋየት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ከፍተኛ ቁጣን መቀስቀሱ ታወቀ

ባሳልፍነው እሁድ ጥር 3-2007 ማለዳ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ ዘመናዊ ሆቴል የሆነው ታሪካዊው ጣይቱ ሆቴል ሙሉ በሙሉ በእሳት የወደመ ሲሆን ድርጊቱ ሆን ተብሎ የታሪክ ጸር በሆነው የወያኔ አገዛዝ ሴራ የተፈጸመ ነው ሲሉ ኢትዮጵያውያን በአገዛዙ ላይ ቁጣቸውን እየገለፁ እንደሚገኙ ዘጋቢያችን ከተለያዩ ማህበራዊ መድረኮች ላይ ያሰባሰባቸውን የህዝብ አስተያየቶች አጠናክሮ ያደረሰን መረጃ ያሳያል። የእሳት አደጋ ብርጌድ መስሪያ ቤት በሆቴሉ አቅራቢያ ሆኖ ሳለ እሳቱ ከተነሳ በትንሹ ለአንድ ሰአት ተኩል ያህል አንድም የእሳት አደጋ መኪና አለመታዬቱና ብሆቴሉ አለመድረሱ በርካቶችን ከማስቆጣቱም ባሻገር በአገዛዙ ሆን ተብሎ የተቀነባበረ ሴራ ለመሆኑ እንደ አንድ አብይ ማስረጃ በስፋት እየተጠቀሰ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ታሪካዊውን የጣይቱ ሆቴል መውደም ተከትሎ ቁጣቸውን በማህበራዊ ገፃቸው ላይ ያሰፈሩት አንድ ግለሰብ እንዳሉት በቅርቡ ለዘመናት በወመዘክር ይገኙ የነበሩ በተለያዩ የአለም ቋንቋዎች የተፃፉ የኢትዮድያን ታሪክ የያዙ መዛግብትና ጽሁፎችን በወያኔ ትዕዛዝ ለስኳር መጠቅለያነት በሚል እንዲሸጡና የቀሩት እንዲቃጠል አደረጉ። ዛሬ ደግሞ በኢትዮድያ ታሪክ የመጀመሪያዉ ሆቴል የሆነዉንና ታሪካዊ ቅርሳችንን የእቴጌ ጣይቱ ሆቴል በተቀነባበረ ሴራ እንዲቃጠል አደረጉ። እነዚህ የባንዳ ዉላጆች በተመሳሳይ የጥፋት ድርጊታቸው በልማት ተብየ ስም የአቡነ ጴጥሮስን ሀዉልት እንዲነሳ አድገዋል፤ ጥንታዊ ገዳማትና አድባራትን አፈራርሰዋል። የቅርስ ምዝገባ በሚል ሰበብ የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን ንዋዬ ቅድሳትና ጽላትን ሳይቀር ለምዕራቡ አለም መቸብቸባቸዉ የአደባባይ ሚስጢር ከሆነ ሰነባብቷል በማለት ይህ የወያኔ ቅርስን የማውደም ሴራ የአገዛዙን ሞት ያፋጥናል ሲሉ ቁጭታቸውን አስፍረዋል።

ሌላኛው ኢትዮጵያዊ በበኩላቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ በማንነትህ፣ በታሪክህ፣ በቅርሥህ ላይ እያላገጡ ያሉት የባንዳ ልጆች እምቢተኝነትህ በዝምታህም፤ በጩኸትም ገብቷቸዋል፣ ከቁጥጥራቸው በላይ ሆኖባቸዋል። የሕዝብ ምሬት ሊገነፍል ጫፍ ላይ መድረሱ ታይቷቸዋል፣ ጨንቋቸዋል፣ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ተንቀጥቅጠዋል፣ ፈርተዋል፣ አሁን ላይ በደመነፍስ ነው እየገዙን ያሉት። ዛሬም እንደትናንቱ የአጥፍቶ አጥፊነት ባህሪያቸውን ነው እየደገሙት ያሉት። የጣይቱ ሆቴል መቃጠል የታሪካዊ ቅርስ ጥላቻቸው ጫፍ መድረስ መገለጫ ነው። አጥፊነታቸው ምን ደረጃ ድረስ እንደሆን ነው የሚያሳየው፣ የአውዳሚነት ባህሪያቸው ለታሪካችንና ለቅርሶቻችን ያላቸውን ጥላቻ ያሳያል። ዛሬ የታሪክ ቅርሥ የሆነው ጣይቱ ሆቴል ወደመ ነገሥ ባለተራው ማን ይሆን ? ሲሉ ቁጭታቸውን በጥያቄ ደምድመዋል።

የፋሽስቱ ወያኔን ከዚህ በላይ የምንታገስ ከሆነ ነገ ምንም ዓይነት የታሪክ አሻራ አናገኝም በማለት ቁጭታቸውን ያሰፈሩት ሌላኛው በድርጊቱ የተቆጩ ግለሰብ በበኩላቸው አምባገነኑ ወያኔ ታሪክን በጠራራ ፀሐይ ማቃጠሉን አሁንም ቀጥሎበታል። በዛሬው እለት በኢትዮጵያ የሆቴሎች ታሪክ የመጀመሪያውን የታሪክ ቤተ መዘክር የሆነውን የጣይቱ ሆቴልን እሳት ለኩሰው አጋይተውታል። እነዚህ የአገር ነቀርሳዎች እሳቱን ለኩሰው ሰዎች ገብተው እንዳያጠፉ ፖሊስ በቆመጥ እየጎመደ አባረረ፤ ዐይናችን እያየ ታሪካችን ሲቃጥል ተመለከትን። የእሳት አደጋ መከላከያ በሁለት መቶ ሜትር ርቀት ላይ እያለ በአራቱም አቅጣጫ እሳቱን ለማጥፋት አመቺ ቦታ ላይ ተቀምጦ ሆቴሉ ሙሉ በሙሉ እስኪወድም ድረስ የውሸት ቋት በሆነው ቴሌቪዢናቸው ገና እሳቱን አልተቆጣጠርነውም እያለ በህዝብ ሲሳለቅብ ተመለከትን። ያሳዝናል። በነገራችን ላይ ባለፈው ጊዜ ይህ ሆቴል በመልሶ ማልማት ስም እንዲፈርስ ወያኔ ወስኖ ነበር፤ ሕዝቡ ቁጣውን ሲያሰማ ግን ጊዜ ጠብቆ አቃጥለውታል ። ከዚህ በላይ ወያኔን መታገስ አገራችንና እና ታሪኳን ከፋሽስቶች ጋር አብሮ እንደማጥፋት ነው የማየው። ከዚህ በላይ የሃገራችንን ጥፋት ለማየት መፍቀድ ከባንዳነትም በላይ ባንዳነት ነው ሲሉ ግለሰቡ በጋራ የታሪክና የቅርስ ጸር የሆነውን የወያኔ አገዛዝ ለማስወገድ እንነሳ በማለት ወገናዊ ጥሪያቸውን በማቅረብ መልዕክታቸውን አስተላልፍዋል።

# ኢትዮጵያ የማን ነች?

“ኢትዮጵያ የማን አገር ነች” የሚል ጥያቄ ከዚህም ከዚያም እየተሰማ ነው። ህወሃቶች ከፈጠሯቸው ቀውሶች መካከል አንዱ ይሄው ነው። ዜጎች የአገር አልባነት ስሜት ውስጥ ገብተው የገዛ አገራቸውን “የማን ነች” ብለው እንዲጠይቁ መገደዳቸው።

ለኢትዮጵያዊያኑ ኢትዮጵያ አገራቸው እየሆነችላቸው አይደለም። ኢትዮጵያዊ መሆን ወንጀል እስኪመስል ድረስ በዜጎች ላይ ግፍ እየተፈፀመ ነው። የሚፈፀመው የግፍ ዓይነት ወሰን የለውም። ግማሹ በጠራራ ፀሃይ ደሙ እንዲፈስ ይደረጋል። ሌላው ለቁም ስቃይ ወደ ወይኒ ይጋዛል። ቀሪውም እትብቱ የተቀበረበትን አገር ትቶ ለመሰደድ ይገደዳል። በአገሪቷ ውስጥ የሚፈፀመውን ወሰን አልባ በደል የተመለከቱ ኢትዮጵያን ከውዳቂ መንግስታት ተራ መድበዋታል። በኢትዮጵያችን የዜጎችን መብት አስከብሮ ለመምራት ብቃት ያለው መንግስት ባለመኖሩ እጣ ፈንታችን እንዲህ ከውዳቂ አገራት ተርታ መግባት ሁኗል።

ኢትዮጵያን ለመምራት ብቃት ያለው መንግስት ቢኖር ኑሮ ለረዥም ዘመን በሰላም ተጎራብተው ይኖሩ በነበሩ ህዝቦች መካከል ግጭት ተፈጠረ መባልን ባልሰማን ነበር።ህወሃት አገሪቷን ከተቆጣጠረ ዘመን ጀምሮ ሆን ተብሎ በሚፈጠር ግጭት ብዙ ደም ፈሷል። አማራው ከኦሮሞው፤ ትግሬው ከአማራው እና ከአፋሩ፤ ሶማሌው ከኦሮሞ፤ኦሮሞው ከጉጂው፤ ኑዌር ከአኙዋክ፤ ዲዚ ከሱርማ፤ ሌሎችም ብዙ ግጭቶች በየቀየው ተፈጥረው አይተናል። የብዙ ዜጎችም ህይወት ተቀጥፏል። ይሄ ሁሉ ደም መፋሰስ የሚከሰተው ህወሃት ከህዝብ ፈቃድ ያልሆነ እና ከህዝቡ የተለየ በመሆኑ ነው።

ህወሃቶች ከህዝብ የተለዩ ብቻ ሳይሆኑ የህዝብ ጠላት መሆንን የመረጡ ብድኖች ስለመሆናቸው ብዙ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል። ህወሃቶች “አማራና ተፈጥሮ” የትግራይ ህዝብ ጠላቶች ናቸው ብለው መፃፋቸው እና ማስተማራቸው የህዝብ ጠላት መሆንን ስለመምረጣቸው ቋሚ ምስክር ነው። ህወሃቶች በስልጣን የሚያቆየን በህዝቦች መካከል የሚፈጠረው አለመተማመንና የጠላትነት ስሜት ብቻ ነው ብለው ከልባቸው ያምናሉ። በህዝቦች መካከል የሚፈጠረው አብሮነት፤ አብሮነቱን ለማዘመን የሚረዳ መተማመን፤ ይሄም የሚወልደው አንድነትና ህብረት በህወሃት ዘንድ የሚወደድ ነገር አይደለም። በህወሃት ዘንድ የሚወደደው በህዝብ መካከል የሚፈጠረው የአለመተማመን ስሜት ይህም አለመተማመን የሚወልደው ግጭት ነው። ግጭት ተፈጥሮ የንፁህ ደም ሲፈስ በህወሃቶች መንደር ደስታ ይሆናል።በዜጎቹ ግጭት እና ደም መፋሰስ ተደስቶ የሚኖር ቡድን እንደ ህወሃት ዓይነት በየትም አገር ታይቶ አይታወቅም።

ከሰሞኑ በአማራ ክልል ነዋሪዎችና በትግራይ ክልል ነዋሪዎች መካከል ግጭት ተከሰተ መባልን ሰምተናል። ይሄ በጣም አሳፋሪና አሳዛኝ ነገር ነው። ህወሃት ከመፈጠሩ በፊት በሠላም ተጎራብቶ የሚኖር ህዝብ ዛሬ ደም መፋሰስ ደረጃ ወደ ሚያደርሰው ግጭት ተሻግሮ መስማታችን አሳፋሪ ነው። ህወሃቶች ከመቸውም ግዜ በላይ የኢትዮጵያ አንድነት ተጠናክሯል እያሉ ሳይታክቱ በሚያወሩበት በዚህ ግዜ አብሮ ለብዙ ዘመን የኖር ህዝብ ወደ ግጭት የመግባቱ ነገር የህወሃቶች ትሩፋት ሁኖ እናገኘዋለን። ህወሃቶች በዘመናቸው ካተረፉልን ቀውሶች መካከል ሳይጠቀስ የማይታለፈው በህዝቦች መካከል የሚፈጥሩት ግጭት ነው። በህዝቦች መካከል በሚፈጠረው ግጭት ብቻ እድሜያችን ይረዝማል ብለው ማመናቸው ህወሃቶች የገበቡት የክፋት አዘቀት ምን ያክል ጥልቅ እንደሆነ ያሰየናል።

ጥላቻ ለህወሃቶች የመኖሪያቸው ድንኳን ሁኖ አቆይቷቸዋል። ከእነርሱ ያልሆኑት በሙሉ ከጠላትነት በታች ስፍራ የላቸውም። ሁሉንም ጠላት አድርጎ ማየት ደግሞ ከፍርሃት እና በራስ ላይ ዕምነት ከማጣት የሚመነጭ መሆኑ ይታወቃል። አሁን አሁን እነዚህ ቡድኖች ፍራቻቸው ፈሩን ለቆ የራሳቸውን ጥላ የመፍራት ደረጃ ላይ ደርሰዋል። የራሱን ጥላ መፍራት የጀመረ ቡድን ራዕይ ኖሮት በሰከነ መንፈስ አገርን የመሰለ ትልቅ ነገር ለመምራት ብቃት አይኖረውም። ህወሃቶች አስቀድሞ በነበርው የአቅም ማነስ ተግዳሮታቸው ላይ ፍርሃት ታክሎበት አገሪቷን ወደ ከፋ ሁኔታ ሊወስዷት እየሞከሩ ነው።

ለህወሃቶች አገር ማጥፋት ጀግንነት ሁኖ እንደሚቆጠር ድርሳናቶቻቸው ይመሰክራሉ። ለምስሌ *“እኛ ከሌለን አገሪቷን እንበትናታለን”* የሚለው ሟርት በእያንዳንዱ የጥፋት ቡድኑ አባል ልብ ውስጥ የተፃፈ ሃሳብ ነው። ከዚህ በላይ አገር የሚያጠፋ ሃሳብ የለም።” እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል” የሚሉ ቡድኖች በአገሪቷ ጫንቃ ላይ ተቀምጠው ስለ ሰላምና እድገት ማውራት ፈፅሞ አይቻልም። ሠላም ማለት የጦርነት አለመኖር ማለት አይደለም፤ ልማትም ሰማይ ጠቀስ ፎቆችን ማቆም ማለት አይደለም። ሠላምም ሆነ ልማት ህወሃቶች ከሚያወሩት የተለየ የአስተሳሰብ ደርዝ ያለው ትልቅ ፅንሰ ሃሳብ ነው። ህወሃቶች ይህን ትልቅ ትርጉም ያለውን ቁም ነገር ለመረዳት አዕምሮአቸው የተከፈተ አይደለም። በክፉ አስተሳሰባቸው ተተብትበተው፤ ከቂምና በቀል ራሳቸውን መለየት አቅቷቸው ራሳቸው ለራሳቸው የገነቧቸውን ህንፃዎች እየቆጠሩ ኢትዮጵያ በልማት እየገሰገሰች ነች ይሉናል። ዕለት ዕለት የንፁህ ሰው ደም እያፈሰሱ ከመቸውም ግዜ በላይ ሠላማችን ተጠብቋል ሲሉም ፈፅሞ አያፍሩም። ይህን ወሬያቸውን እውነት ነው ብለን እንድንቀበል የሚያደርገን አንዳችም እውነት የለም። ህወሃቶች የሃሰት ልጆች በመሆናቸው መዋሸት በእነርሱ ዘንድ የፖለቲካ ጥበብ ነውና በትልቁም በትንሹም ይዋሻሉ።

ለእነዚህ የጥፋት ቡድኖች የልማትንና የሠላምን ምንነት ለማስተማር መሞከር በጭንጫ መሬት ላይ መልካም ዘርን እንደመዝራት ይሆንብናል።የህወሃቶች አዕምሮ በጎ ነገር የማይዘልቅበት ፍፁም ጭንጫ ሁኗል። እነዚህ ቡድኖች ከህዝቡ ሁሉ በላይ ጠቢብ የሆኑ ይመስላቸዋል። እንደ ፈጣሪ ቃል እነርሱ ያሉት ካልሆነ ህዝቡ ሁሉ ቢጠፋ ግድ እስከማይኖራቸው ድረስ በትዕቢት ታውረዋል። ትዕቢተኛ ቡድን አገርንና ህዝብን ያጠፋል እንጂ አያለማም። ደም መፋሰስን ያበዛል እንጂ ሠላምን አያመጣም።የህወሃቶች የስንፍናቸው ብዛት የወለደው ግጭት አብሮ በኖረው ወደፊትም አብሮ መኖር በሚችለው ህዝብ መካከል ደም እያፋሰሰ ነው።በቅርቡ በአማራ እና በትግራይ ክልል ድንበር አካባቢ ተነስቶ የሰው ህይወት ያለፈበትን ግጭት ምሳሌ አድርጎ ማቅረብ ይቻላል።

በአጠቃላይ ህወሃቶች በአገሪቷ ጫንቃ ላይ እስካሉ ድረስ ሠላምም ሆነ ልማት ተብሎ ሊጠራ የሚችል ነገር በኢትዮጵያችን አይኖርም። እነዚህን የጥፋት ልጆች ከቅዥታቸው ነቅተው ከሰው መሃል ሁነው እንደ ሰው ልጅ ያስባሉ ብሎ መጠበቅም ከንቱ ምኞት ነው። ለብዙ ዘመን ከዛሬ ነገ ከቅዥታቸው ነቅተው ሰው ይሆናሉ ብለን ስንመኝ ነበር። የቻሉትን ያክል ዘርፈው በቃኝ ይሉ ይሆናል የሚልም ተስፋ ነበረ። ምኞታችንና ተስፋችን ግን እንዲሁ በከንቱ ውሃ በልቶት ቀርቷል። በጎ ምኞታችንን የሚገዳደሩን ኃይሎች በወንበሩ ተቀምጠው ፈራጅ ሆነው ሳለ፤ ተስፋችንን በሚያመክኑ ቡድኖች እግር ተወርች ታስረን እያየን ዝም ብለን እንኖር ዘንድ ሰው መሆናችን ሊከለክለን ይገባል።አዎን ሰው መሆናችን ብቻ ህወሃቶች የሚፈፅሙትን እኩይ ተግባር ለማስቆም እንድንነሳ ያደርገናልና ሁላችንም አብረን ተነስተን በፍርድ ወንበር የተቀመጡ ክፉዎችን አደብ እናስገዛለን።

ህወሃቶች አገር አጥፊ ኃይሎች እንደሆኑ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ የሚስማማበት እውነት ሁኗል። ከዚህ እውነት ለጥቆ የሚያሳስበን ብርቱ ነገር በዚያች አገር እጅግ በጣም ብዙ አደር ባዮች የመፈጠራቸው ነገር ነው።”*እኛ ምን እናድርግ ታዘን ነው እንዲህና እንዲያ የምናደርገው* “የሚሉ የሂሊና ሙግት የሌለባቸው ዜጎች በዚያች አገር የመብዛታቸው ነገር አሳሳቢ ነው። ሰው ለቁሳቁስ፤ ለሚበላና ለሚጠጣ ኃላፊ ነገር ብሎ የወንድሙን ደም ማፍሰስ ሲጀምር ያን ግዜ አገር መፍረስ ትጀምራለች። በተለይም እንዲህ ዓይነቱ ነውር ድርጊት በህግ አስከባሪው አካል መፈፀም ሲጀምር አንድ አገር እንደ አገር የመቀጠሏ ሁኔታ አደጋ ላይ ይወድቃል። ዛሬ በኢትዮያችን የፍርድ ቤት ወንበሮች በምናምንቴዎች ተይዘዋል፤ የፍትህ መዶሻዎችም በጨካኞችና በሃሰተኛ ልጆች እጅ ወድቀዋል። አገርንና ህዝብን ለመጠበቅ የተሰለፉ ኃይሎች የህዝባቸውን ደም በከንቱ የሚያፈሱ ሁነዋል። የፖሊስ ኃይሉም የዘራፊዎችንና የነፍሰ ገዳዩን ቡድን የሚጠብቅ እንጂ የዜጎችን ሠላም የሚጠብቅ ሊሆን አልቻለም። እነዚህ ኃይሎች ከሂሊናቸው በላይ ለሥጋቸው እንዲገዙ የሚያደርጋቸው ምን እንደሆነ ባናውቅም አደር ባይነታቸው አገርንና ህዝብን በብርቱ እየጎዳ እንደሆነ መካድ አይቻልም።

ታዝዤ የገዛ ወገኔን ገደልኩ የሚል የመከላከያ ኃይል አባል፤ ታዝዤ በሃሰት ማስረጃ ክስ መሰረትኩ የሚል ፖሊስ እና አቃቤ ህግ ፤ታዝዤ በሃሰት ማስረጃ ፈረድኩ የሚል ዳኛ ነገ የሚያስጠይቅ ዘመን ሲመጣ ማምለጫ ምክንያት እንደማይኖረው ሊገነዘበው ይገባል። ታዞ ወንጀል መፈፀም ከወንጀሉ ነፃ አያደርግም። በተለይም በህግ አስከባሪውና አስፈፃሚው አካል ይህን መሰሉ ነውር ሲፈፀም ማየት ለኢትዮጵያችን ትልቅ ውድቀት መሆኑን እነዚሁ አካላት እንዲያውቁት ያስፈልጋል።ታዞ ደግሞ ደጋግሞ ወንጀል መፈፀም ከአደር ባይነት በላይ የሆነ ራሱን የቻለ ወንጀል ነው። በንፁሃን ላይ ወንጀል ሲፈፀም አይቶ እንዳላዩ መሆን፤ ሰምቶም እንዳልሰሙ መምሰል አደር ባይነት ሊባል ይችላል ታዞ የገዛ ወገንን መግደል ግን ወንጀል መሆኑን ማወቅ ይገባል። ኢትዮጵያችን ከገጠሟት ቀውሶች መካከል አንዱ ነፍሰ ገዳዮችን እያዩ ዝም የሚሉ አደር ባዮች የመበራከት ነገር ነው። ከትላልቅ የኃይማኖት መሪዎች አንስቶ እስከ ተራው ምዕመን ድረስ ያለው ኃይል በዚህ እርግማን የተያዘ እስኪመስል ድረስ በዝምታ ተውጧል።ይህ ዝምታ የሚሰበርበት ግዜ እሩቅ አለመሆኑን ስንናገር በህወሃቶች ዘንድ ድንጋጤ እንደሚሆን እናውቃለን። እናም ዝምታው ይሰበራል።ዜጎችም ለፍትህ፤ለእኩልነት እና ለነፃነት የሚያደርጉትን ትግል አፋፍመው ይቀጥላሉ። እስከ ህይወት መስዋዕትነት ድረስ ለመክፈል የተዘጋጁ ወጣቶች ሰይፋቸውን ከሰገባው መዘዋል።

ግንቦት ሰባት ንቅናቄም የጥፋት ኃይል መሆንን ምርጫቸው ያደረጉ ህወሃቶች የገነቡትን የጥፋት መረብ እንበጣጥሰዋለን። በወገኖች መካከል የሚፈጠረው ግጭት የመኖሪያቸው ድንኳን የሆናቸው የጥፋት ኃይሎችን አደብ ለማስገዛት የሚከፈለውን መስዋዕትነት ለመክፈል እየሰራን ነው። ህወሃቶች ሆይ በዜጎች ደም እየቀለዳችሁ አትቀጥሉም። በተገኘው አጋጣሚ በተገኛችሁበት አምባ ሁሉ እንታገላችኋለን። በሚገባችሁ ቋንቋም እናናግራችኋለን። ደግሞም እውነት ከእኛ ዘንድ ስላለ አለ ምንም ጥርጥር እናሸንፋችኋለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!**

## በደቡብ ጎንደር ዞን የተቀሰቀሰው ግጭት ተባብሶ ቀጥሏል

በእስካሁኑ ከባድ የተኩስ ልውውጥ 5 የአካባቢው ሚሊሻዎች ሲገደሉ ከ 8 በላይ የሚሆኑት ደግሞ ከባድ የመቁሰል አደጋ እንደደረሰባቸው ከስፍራው የደረሰን መረጃ ያመለክታል።

እብሪተኛው ወያኔ በደቡብ ጎንደር ዞን በሊቦ ከምከም ወረዳ እያደረሰ በሚገኘው መጠነ ሰፊ ጭቆና፤ በደልና የሰብአዊ መብት ጥሰቶች የተንገፈገፉ የአካባቢው ተወላጆች ወደ ጫካ እየከተቱ ሲሆን በዚህ በያዝነው ሳምንት መጀመሪያ ጀምሮ የአካባቢው ተወላጆች ከወያኔ ሚሊሻና ልዩ ሃይል ጋር ከባድ ግጭት ወስጥ መግባታቸው ታውቋል። ከግጭቱ ጋር ተያይዞ በተቀሰቀሰው ከባድ የተኩስ ልውውጥ 5 ሚሊሻዎች ሲገደሉ ከ 8 በላይ የሚሆኑት ደግሞ ከባድ የመቁሰል አደጋ የደረሰባቸው ሲሆን 8 ቤቶች በከባድ መሳሪያ መጋየታቸውን ለማወቅ ችለናል። ወረዳዋን ጨምሮ በአጠቃላይ በዞኑ አሁን ድረስ ከባድ ውጥረት ነግሶ መቀጠሉ የተገለጸ ሲሆን የአካባቢው ተወላጆች በህብረተሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ድጋፍ እየተቸራቸው እንደሚገኝ ታውቋል። በዞኑ በርካታ ወጣቶችና ጎልማሶች ጫካ የከተቱ ወገኖቻቸውን በስፋት እየተቀላቀሏቸው እንደሚገኙም የደረሰን መረጃ ያሳያል። በተኩስ ልውውጡ መራራ ሽንፈትን እየተጎናጨ የሚገኘው እብሪተኛው የወያኔ አገዛዝ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ልዩ አጋዚ ጦር ወደ አካባቢው ማንቀሳቀሱን ተከትሎ ግጭቱ ወደ ከፍተኛ ደም አፋሳሽ ጦርነት ሊያመራ ይችላል የሚል ስጋት በዞኑ አንዣቧል እንደሚገኝ ለማወቅ ችለናል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በአካባቢው ህብረተሰብ ዘንድ በጀግንነቱና በፈጸመባቸው የጦር ጀብዶዎችና ድሎች እየተወደሰ የሚገኘው አረጋ የተባለ ግለሰብ እስከ ተከታይ ወንድሞቹ ጫካ የከተተውን ሐይል እየመሩ እንደሚገኙ ለማወቅ ተችሏል። በግጭቱ እየደረሰባቸው ባለው መራራ ሽንፈት የተበሳጩት የፋሺስቱ ወያኔ የአካባቢው ቅጥረኛ ሚሊሻዎች የአረጋን መነኩሴ እናት እጅግ አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ በጥይት ደብድበው ከገደሉ በኋላ ቤታቸውን በከባድ መሳሪያ ማቃጠላቸውን መዘገባችን ይታወሳል።

## በጣይቱ ሆቴል የእሳት አደጋ የተፈጠረው ቁጭት በአገር ቤት አድማሱን አስፍቶ ቀጥሏል

የፋሽስቱ ወያኔ ሴራ እንደሆነ በስፋት እየተነገረ ባለው የእቴጌ ጣይቱ ሆቴል ቃጠሎ የተፈጠረው ቁጭት በኢትዮጵያ አድማሱን አስፍቶ መቀጠሉን በየ ስፍራው የሚገኙ ተባባሪ ዘጋቢዎቻችን ለሬዲዮ ክፍላችን የላኩት መረጃ ያመለክታል። በአገር ቤት የሚኖሩ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ለተባባሪ ዘጋቢዎቻችን እንደተናገሩት በሆቴሉ የደረሰው የእሳት አደጋ ሆን ተብሎ በፋሺስቱ ወያኔ የተደረገ እኩይ ሴራ መሆኑን አስረግጠው እየተናገሩ ሲሆን ሲሆን ለአብነትም ዘረኛው ህወሓት ባለፉት 24 አመታት በኢትዮጵያ እያደረሰ ያለውን የታሪካዊ ቅርሶች ውድመት ለአብነት እያጣቀሱ በማስረጃነት ተናግረዋል። በጸረ ኢትዮጵያው የህወሃት አገዛዝ ትዕዛዝ በቅርቡ በብሄራዊ ወመዘክርን የደረሰውን የኢትዮጵያን ታሪክ የያዙ መዛግብትን የማውደም እንቅስቃሴን ጨምሮ ሌሎችንም በአገዛዙ እኩይ ሴራ የጠፉ ታሪካዊ ቅርሶቻችንን እና ጥንታዊ ገዳማት፤ አድባራት፤ ጥንታዊ መስጊዶች፤ የቤተ ክርስቲያን ንዋዬ ቅድሳትና ጽላትን በአስረጅነት በኢትዮጵያውያን ከተጠቀሱት መካከል እንደሚገኙበት ዘጋቢዎቻችን አመልክተዋል።

የጣይቱ ሆቴል በእሳት መውደም ፋሺስታዊው የወያኔ አገዛዝ ለታሪካዊ ቅርሶቻችን ያለውን ጭፍን ጥላቻ ዳግም ያረጋገጥንበት ነው የሚሉት ኢትዮጵያውያን ታሪክ ሲወድም ቁጭ ብለን መመልከታችን የጥፋቱ ተባባሪ ከመሆን አይተናነስምና አገራችንን ከነ አኩሪይ ታሪክና ቅርሶቿ ጠብቀን ከትውልድ ትውልድ ለማሸጋገር ጸረ ታሪክና ቅርስ የሆነውን የህወሓት አገዛዝ ለማስዉገድ ልንረባረብ የምንገባበት ወሳኝ ምዕራፍ ላይ እንገኛለንና በጋራ እንነሳ ሲሉ መልዕክታቸውን ያስተላለፉ ጥቂቶች አለመሆናቸው በዘገባው ተመልክቷል።

በሌላ ዜና የጉጅሌው ወያኔ አገዛዝ ከመጭው የ 2007 አገራዊ ምርጫ ጋር ተያይዞ ሊቀሰቀስ የሚችለውን ህዝባዊ ተቃውሞና አመጽ ለማፈን በሚል ልዩ የአጋዚ ጦር ማቋቋሙን ለማወቅ ችለናል። ልዩ የአጋዚ ጦሩ በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች የተበተነ ሲሆን አስፋላጊ በሆነ ጊዜ በህዝብ ላይ ማንኛውም አይነት የሐይል እርምጃ እንዲወስዱ በቱባ ጉጅሌዎች ትዕዛዝ እንደተሰጣቸው ታውቋል። በኢትዮጵያ በተለይ በምርጫ 97 በፋሽስቱ ወያኔ የተቋቋመው ልዩ የአጋዚ ጦር ድምፃችን ይከበር ብለው አደባባይ የወጡ ንጹሃን ኢትዮጵያውያን ላይ የወሰደው አሰቃቂ እርምጃ የሚታወስ ሲሆን በአዲስ አበባ ብቻ ከ 200 በላይ ሰዎች ግንባራቸው በስናፐር ጥይት ተቦድሶ መገደላቸው መቼውንም አይዘነጋም። በተያያዘ ዜና መጭውን የይስሙላ ምርጫ የአውሮፓ ህብረትን ጨምሮ ሌሎች አለማቀፍ ተቋማት በታዛቢነት እንደማይሳተፉ መግለፃቸው የሚታወስ ሲሆን ፋሺስቱ ወያኔ በአገር ቤት የሚንቀሳቀሱ ጠንካራና ሰፊ የህዝብ ድጋፍ ያላቸውን የተቃዋሚ ፓርቲዎች ከምርጫው ውድድር ለማስወጣት እየተንቀሳቀሰ እንደሚገኝም ለማወቅ ችለናል።

## የሰማያዊ ቲሸርት የለበሱ ወጣቶች ከሥላሴ በዓል ላይ ተባረሩ፤ የጥምቀት በዓል በዉጥረት ታጀቦ እየመጣ ነዉ

የዓመቱን የሥላሴ በዓል ለማክበር አራት ኪሎ የሚገኘው ቅድስት ስላሴ ካቴድራል ቤተ ክርስቲያን የተገኙ ወጣቶች ሰማያዊ ቲሸርት በመልበሳቸው በፖሊስ መባረራቸውን ነገረ- ኢትዮጲያ ዘግቧል።ፖሊስ፤ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅስ የተጻፈበት ሰማያዊ ቲሸርት የለበሱትን ወጣቶች ቲሸርቱን እንዲያወልቁ ሲጠይቅ ወጣቶቹ አናወልቅም በማለታቸው ከበዓሉ እንዳባረራቸው የዐይን እማኞች ገልጸዋል። ከተባረሩት ወጣቶች መካከል አብዛኛዎቹ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚገቡትንና የሚወጡትን ምእመናን በማስተባበር ላይ እንደነበሩ የተገለጸ ሲሆን ፤ ወጣቶቹ -ይታሰሩ፤ አይታሰሩ እስካሁን የታወቀ ነገር የለም።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፤ ከአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን የመጡ ከፍተኛ ኃላፊዎች ለጥምቀት በዓል ሰማያዊ ቲሸርት ያዘጋጁትን የጃንሜዳ እና አካባቢው የጥምቀት በዓል አስተባባሪዎችን በመሰብሰብ፣ ወጣቶች ያዘጋጇቸውን ሰማያዊ ቲሸርቶች በዓሉ ላይ እንዳይለበሱ በተደጋጋሚ እያስጠነቀቁ ይገኛሉ።በፖሊሶችና በደህንነቶች ተደጋጋሚ ጫና የጃንሜዳ አካባቢ ወጣቶች ያዘጋጁትን ሰማያዊ ቲሸርትና በቲሸርቱ ላይ ያጻፉትን ጥቅስ መቀየራቸውን ሲናገሩ፤ በአንጻሩ የፈረንሳይና ቤላ አካባቢ ወጣቶች፤ "ሰማያዊ ቲሸርታችንን አንቀይርም!" በሚል አቋማቸው መጽናታቸው ታውቋል።

ትናንት ጥር 6 ቀን የአዲስ አበባ መስሪያ ቤቶችና ወረዳዎች ኮሙኒኬሽን ኃላፊዎች፤ በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ባደረጉት ስብሰባ፤ የየካ ክፍለ ከተማ ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ኃላፊ "ሰማያዊ ፓርቲ ፈረንሳይ ሌጋሲዮን አካባቢ ‹የፈራ ይመለስ› የሚል ሰማያዊ ቲሸርት አስለብሶ ሲበጠብጠኝ ሰንብቷል።" ሲሉ ሪፖርት ማቅረባቸውን የስብሰባው ተሳታፊዎች ለጋዜጣው ገልጸዋል።

ስለ ጉዳዩ የተጠየቁት የሰማያዊ ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ዮናታን ተስፋዬ፡- "ደህንነት፣ ፖሊሶችና ካድሬዎች እያንዳንዱን የህዝብ እንቅስቃሴ ከሰማያዊ ፓርቲ ጋር በማገናኘት ወቀሳ የሚያቀርቡት፤ ህዝብ ውስጥ ብሶት እንዳለ እና ሰማያዊም የህዝብን ብሶት እንደሚያሳማ ስለሚያውቁ፣ ከምንም በላይ ገዥው ፓርቲ የራሱን ጥላ የማያምንበት ደረጃ ላይ ስለደረሰ ነው" ብለዋል። የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የመብት ጥያቄ ባነሱባቸው ጊዜያት ሁሉ ገዥው ፓርቲ ሰማያዊ ፓርቲን "የሙስሊም ፓርቲ ነው" የሚል ሀሰተኛ ወሬ ሲያሰራጭ እንደነበር ያስታወሱት ኃላፊው፤ "አሁንም ፓርቲውን ከእያንዳንዱ የህዝብ እንቅስቃሴ ጋር እያገናኘ ቢበረግግ አያስገርምም" ብለዋል።

## የኢሳት ጋዜጠኛ የወንድማገኝ ጋሹ ባለቤትና ሶስት ልጆች ከኢትዮጲያ ተባረሩ

የሶስት ዓመት ህጻንን ጨምሮ ከሶስት ህጻናት ልጆች ጋር ለእህቷ ስርግ ወደ ኢትዮጲያ አቅንታ የነበረችውና ላለፉት 20 ቀናት በአዲስ አበባ የቆየችው ወይዘሮ አበባ፤ ከነ ልጆቿ ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ታስራ እንድታድር ከተደረገች በሁዋላ ነው ከሀገር የተባረረችው።በእህቷ ሰርግ ላይ በርካታ ደህንነቶች ሲከታተሏት እንደነበረ የገለጸችው ወይዘሮ አበባ፤ በማግስቱ በቤተሰቦቿ ቤት ሳለች ሁለት ደህንነቶችና አራት ፖሊሶች በመምጣት ከሶስት ዓመት ህጻን ልጇ ጋር እያዋከቡ ወደ አውሮፕላን ማረፊያ ይዘዋት እንደሄዱና እዛ ባለ ቢሯቸው ውስጥ እንዳሰሯት ተናግራለች። ደህንነቶቹ አክለውም "ወንጀለኛ ነሽ፤ ባለቤትሽ ኢሳት ላይ መስራት እስካላቆመ ድረስ ኢትዮጲያ የመኖር መብት የለሽም እንዳሏት ተናግራለች።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## በኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባርና የግንቦት 7፣ ለፍትህ፣ ዴሞክራሲና የነጻነት፣ ንቅናቄ መህል ... ( ከገጽ 1 የዞረ )

አርበኞችና ግንቦት 7፣ የደረሱበት የውህደት ውሳኔ ወይም በሌሎች በጋራ ሊያሰሩ በሚችሉ ስምምነቶች አብሮ ለመስራት መወሰን የማይችልበት ምንም ምክንያት አይታየንም። በወያኔ አድሎ ስርዓት የተንገፈገፈና ትግሉን ለመቀላቀል የቆረጠ ማንኛውም ዜጋ፣ የተገኘውን አጋጣሚ በመጠቀም ትግሉን መቀላቀል ይችላል፣ የኢትዮያ ሕዝብ በአንድነት የተነሳ ቀን ደግሞ፣ የወያኔ ግብዓተ መሬት ይፈጸማል፣ ብለን ከልብ እናምናለን።
ይህም በመሆኑ፣

**ለተቃዋሚ ድርጅቶች፣**

ዛሬ በአርበኞችና በግንቦት 7፣ የተጀመረው ጉዞ ውጤታማ በመሆን ሀገራዊና ታሪካዊ ትርጉም እንዲኖረው፣ ሌሎችም በተግባር የምትንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ድርጅቶች፣ ወያኔን የማስወገድንና ብሎም ሀገር የማረጋጋቱን ሀላፊነት በጋራ እንድንወጣ የሚያስችል መቀራረብ እንድናደርግ ፣ በውህደት በመሰረትነው፣ በአርበኞች ግንቦት 7፣ ለአንድነትና ዴሞክራሲ፣ ንቅናቄ፣ ሥም፣ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

**ለወታደራዊና የፖሊስ ሠራዊት አባላት፣**

የወያኔ ዘረኛና አምባገነን ቡድን ዕድሜን ለማሳጠርና ሁላችንንም በእኩልነት የምታስተናግድ ሀገር እንድትኖር ፣ በየቦታው የሚደረገውን ትግል፣ የሰሞኑን ቆራጥ የዓየር ሃይል መኮንንኖች ያሳዩትን ዓርያነት በመከተልና በተገኘው አጋጣሚና ሁኔታ በመጠቀም፣ እንድትቀላቀሉ በውህደቱ ድርጅት፣ በአርበኞች ግንቦት 7፣ ለአንድነትና ዴሞክራሲ፣ ንቅናቄ፣ ሥም፣ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

**የተከበርከው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ፣**

በረጅም ታሪክህ አይተሄው ለማታውቀው፣ ውርደት፣ ክፋት፣ የመከፋፈልና የመጋጨት አደጋ፣ የመብት እረገጣና አፈና፣ ሀገርና ሕዝብን የማራከስና የመሸጥ፣ ዕኩይ ተግባር፣ የተጠናወተው ወያኔ እና የግብር አበሮቹን፣ ጠራርጎ ለማስወገድ በተጀመረው የጋራ ትግል ውስጥ በቀጥታ እንድትሳተፍም ሆነ በምትችለው ሁሉ እርዳታ እንድታደርግ፣ በዛሬው ጥር 2 ቀን 2007 ዓ.ም የአርበኞችና የግንቦት 7 ውህደት በወለደው፣ በአርበኞች ግንቦት 7፣ ለአንድነትና ዴሞክራሲ፣ ንቅናቄ ሥም፣ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

**ድል ለኢዮጵያ ሕዝብ!!!**

**አርበኞች ግንቦት 7፣ ለአንድነትና ዴሞክራሲ፣ ንቅናቄ፣**

**ጥር 2 ቀን 2007 ዓ.ም**

## አንድነት ፓርቲ ለዉህደትም ሆነ ለትብብር ዝግጁ መሆኑን ገለጸ

ጥፍኖተ ነጻነት የፓርቲውን የድርጅት ጉዳይ ሀላፊ አቶ ተክሌ በቀለን ጠቅሶ እንደዘገበው፤ የአንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ታህሳስ 25 ቀን 2007 ኣመተ ምህረት ባደረገው ስብሰባ መጪውን ምርጫና ከምርጫው ጋር ተያይዘው ስለሚመጡ ጉዳዮች፤ እንዲሁም ከምርጫው በኋላ ፓርቲዎች ሊኖራቸው ስለሚገባው ትብብርና ውህደት የሚያመቻች ኮሚቴ ተቋቁሟል።በስብሰባው፣ ፓርቲዎች በትብብርና በውህደት መስራት እንዳለባቸው ስራ አስፈጻሚው መምከሩን የተናገሩት አቶ ተክሌ ፤ ፓርቲያቸው ከመድረክ ጋር በትብብር ከሰማያዊና ከመኢአድ ጋር ደግሞ ውህደት ፈጥሮ ለመስራት ዝግጁ መሆኑን አስታውቀዋል።

ተቃዋሚ ፓርቲዎች በገዥው ፓርቲ ላይ ጫና በማሳደር አሁን ካሉበት ደረጃ ወደፊት መሄድ የሚችሉት ተባብረው አለያም ተዋህደው ሲሰሩ ብቻ ነው ብሎ ሚያምነው አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ ፓርቲዎቹ እንዲዋሀዱ አለያም ተባብረው እንዲሰሩ ጥሪ እያደረገ ይገኛል።በተለይ በአሁኑ ወቅት ፓርቲዎቹ በምርጫ ቦርድ አማካይነት እያደረገባቸው ያለውን ከበድ ያለ ጫና ለመቋቋም ቢያንስ ተባብሮ መስራት አስፈላጊ እንደሆነ የሚመክሩ በርካታዎች ናቸው።

በሌላ በኩል ምርጫው በተቃረበበት በአሁኑ ወቅት፡ከፓርቲዎች ጋር ውዝግብ ውስጥ ገባው ምርጫ ቦርድ አንድነትና መኢአድ በሁለት ሳምንት ውስጥ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲያደርጉ ውሳኔ ማሳለፉን እና ለሰማያዊ ፓርቲ ማስጠንቀቂያ ሰጥቻለሁ ማለቱን ነገረ-ኢትዮጵያ ዘግባል።እንደ ጋዜጣው ዘገባ’፤ የቦርዱን ስብሰባ ረግጦ ከመውጣትም በላይ ይቅርታ ለመጠ የቅ ፈቃደኛ አይደለም ላለው ሰማያዊ ፓርቲ የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ መስጠቱን የገለጸው ቦርዱ፤ ፓርቲው ማስጠንቀቂያውን የማያከብር ከሆነ ህጋዊ እርምጃ እወስዳለሁ ሲል ዝቷል።

## ግንቦት 7ና አርበኞች ግንባር ያደረጉት ውህደት ... ( ከገጽ 1 የዞረ )

ስርአት መሰረት የሚጥልም መሆን አለበት ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል። በጉባየው አንድነት ሃይል ነው በውህደቱ የተጀመረው ታሪካዊ ጉዞ ተጠናክሮ ይቀጥላል፤ ውህደቱ የአገራችን የትንሳኤ ምልክት ነው፤ ኢትዮጵያንና ህዝባችንን ከውርደት እንታደጋለን፤ ሞት ለፋሽስቱ ወያኔ፤ አርበኞች ግንቦት 7 ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ ጋር በመሆን የዲሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ትግላችን በደማችን ይረጋገጣል የሚሉና ሌሎች በርካታ መፈክሮች በአዳራሹ ተስተጋብተዋል። ከእንግዲህ መለያየት የለም አንድ ሆነን ኢትዮጵያን ነፃ እናወጣለን ያለው አርበኞች ግንቦት 7 ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ (አግኤደን) ለሌሎች በትጥቅ ትግል የተሰማሩ ድርጅቶችም እንዲቀላቀሉ ጥሪ ማቅረቡን ለማወቅ ችለናል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በትጥቅ ትግል የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝን በማስወገድ የኢትዮጵያን የመከራና የጨለማ ዘመን ለማክሰም የሚንቀሳቀሱት የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር እና የግንቦት 7 ንቅናቄ አንድ የመሆናቸው የብስራት ዜና ይፉ መደረጉን ተከትሎ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ሰፊ መነጋገሪያ ሆኖ ከመቀጠሉም በላይ በሰፊው የኢትዮጵያ ህዝብ ከፍተኛ ድጋፍ እየተቸረው ሲሆን በተቃራኒው ውህደቱ በፋሺስቱ ወያኔ መንደር ከፍተኛ መደናገጥ መፍጠሩን የውስጥ ምንጮቻችን አመልክተዋል። የሁለቱን ድርጅቶች መዋሃድ ተከትሎ ኢትዮጵያውያን በተለያዩ የማህበራዊና የመወያያ መድረኮች ላይ በመገኘት ድጋፍና አጋርነታቸውን እየገለጹ ሲሆን ዲሞክራሲያዊ ሃይሎች በጋራ ሆነው መታገል ባለመቻላቸው በተናጠል ያደርጉት የነበረው የነፃነት ትግል ውጤት ባለማምጣቱ የፋሽስቱ ወያኔ አገዛዝ ለ 24 አመታት በኢትዮጵያ ህዝብ ዘንድ የተለያዩ ሰቆቃዎችን፤ በደሎችንና ግፎችን እየፈጸመ እንዲቀጥል እንዳስቻለው በመጠቆም ይሄ አሁን የተደረገው የሁለቱ ዲሞክራሲያዊ ሐይሎች ውህደት ይህንን ለወያኔ አገዛዝ የተመቻቸ ትግል ከቀልበሱም በላይ የነፃነት ትግሉን ያፋጥናል ሲሉ እምነታቸውን በመግለጽ ላይ እንደሚገኙ ታውቋል። በተጨማሪም በአገር ቤት፤ በውጭና በጎረቤት አገር የሚኖር ማንኛውም አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ከአርበኞች ግንቦት 7 ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ (አግኤደን) ጎን በመሰለፍ የሞራል፤ የገንዘብና የሃሳብ ድጋፍ በመስጠት የዜግነት ግዴታውን እንዲወጣ ነፃነታ ናፋቂ ኢትዮጵያውያ ጥሪ እየቀረቡ እንደሚገኙ ለማወቅ ችለናል።

በመጨረሻም የአርበኞች ግንቦት 7 ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ንቅናቄ በአገራችን ኢትዮጵያ የተንሰራፋውን ዘረኛና በታኝ ስርአት ከህዝብ ጫንቃ ላይ በማውረድና ሕዝባችን ከገባበት አዘቅት በማውጣት የስልጣን ባለቤት የሚሆኑበትን መንገድ ለማመቻቸት በሚደረገው የሞት ሽረት ትግል በጉጅሌው ወያኔ አገዛዝር ስር ተቀጥረው የሚያገለግሉ የመከላከያ ሰራዊት፤ የፖሊስ፤ የሚሊሻ፤ የአየር ሐይል አባላት እንዲሁም በአገዛዙ የተማረሩ በሌሎች ተቋማት ተቀጥረ የሚያገለግሉ ሰራተኞች፤ ገበሬዎች እና አገር ተረካቢ የሆነው ወጣት ትውልድ በነቂስ ወጥቶ እንዲቀላቀልና የታሪካዊው የነፃነት ትግል አካል እንዲሆን ጥሪ ቀርቧል።

## አርበኞች- ግንቦት 7 ለኢትዮጳያ ህዝብ፣ ለመላከያ ሰራዊቱና ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ... ( ከገጽ 1 የዞረ )

ለማሳጠርና ሁላችንንም በእኩልነት የምታስተናግድ ሀገር እንድትኖር፣ የሰሞኑን ቆራጥ የዓየር ሃይል መኮንንኖች ያሳዩትን ዓርያነት በመከተልና በተገኘው አጋጣሚና ሁኔታ በመጠቀም በየቦታው የሚደረገውን ትግል እንድትቀላቀሉ በውህዱ ድርጅታችን ሥም፣ ጥሪያችንን እናቀርባለን።”ብሏል። ንቅናቄው በመጨረሻም፡-”የተከበርከው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ፣በረጅም ታሪክህ አይተሄው ለማታውቀው ውርደት፣ ክፋት፣ የመከፋፈልና የመጋጨት አደጋ የዳረገህን እና ሀገርና ሕዝብን የማራከስና የመሸጥ ዕኩይ ተግባር የተጠናወተውን አገዛዝ ከነግብር አበሮቹ ጠራርጎ ለማስወገድ በተጀመረው የጋራ ትግል ውስጥ በቀጥታ እንድትሳተፍ አለያም በምትችለው ቀዳዳ ሁሉ ድጋፍ እንድታደርግ፣ በአርበኞች ግንቦት 7፣ ለአንድነትና ዴሞክራሲ፣ ንቅናቄ ሥም፣ ጥሪያችንን እናቀርባለን።” ሲል መግለጫውን ቋጭቷል።